# የግንቦት 7 ወደ አገር ቤት መግባት ፍንደቃ ወደ ኢ-ፍንደቃ ተቀየረ

# (from euphoria to dysphoria)

ወልደአብ ደንቡ

መስከረም **16/2011 -26/9/2018**

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በሴፕቴምበር 9/2018 በአዲስ አበባ ኳስ ሜዳ/እስታዲየም ንግግር ሲያደርግ የነበረው የሕዝብ ብዛትና የህዝቡ ስሜት ምን ይመስል እንደነበረ የተመለከትኩት፣ ንግግሩንም የሰማሁት -ከሶስት ቀናት በፊት በጉጉል ጎልጉዬ ነው ። ለምን ያን ያህል ዘገየህ የሚለኝ ካለ ፤ መልሴ አንተ/አንቺ የእኔ ኑሮ አትኖሩም ነው ።

1.ወያኔዎችና አስመሳይ ታጋዮችን ከመደብደቡ ባሻገር- ንግግሩ ዲፕሎማሲያዊ ወይም የሕዝብ ስሜት የሚስብ ነበር። እንደ ሌላ ግዜ የተንጠራራ፣የተቆነነ (high hat, cocky, pompous etc).አልነበረም

2.የነበረው የሕዝብ ብዛት -የሕዝባዊ አርበኝነትና ሕዝብ ተቀብሎኛልነትን ምቾት የተሰማው ይመስል ነበር

3..የዶክተር ብርሃኑን ንግግር አዳምጣችሁ ከእዚ ጽሁፍ ጋር የለጠፍኩትን ጽሁፍ አንብቡ

### *(FROM DICTATORSHIP TO DEMOCRACY; A CONCEPTUAL FRAME WORK FOR LIBERATION:FOURTH U.S.EDITION, 93 pages) BY GENE SHARP*

ከአምባገነን አገዛዝ ወደ ዲሞክራሲ ጽንሰ -ሃሳባዊ ማዕቀፍ ለነጻነት በጂኒ ሻርፐ ከተሰኘ ጽሁፍ የወሰድኩት ነው ።

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከመታሰሩ በፊት, ግንቦት 7 ስለፈጸማቸው ተግባራት ሲናገር ይህ ጽሁፍ ወደ አማርኛ የተርጎሙት እነሱ ግንቦት ሰባቶች እንደሆኑ ጉራ ሲነፋ ሰምቼው ነበር ።

የመጽሃፉ ተርጓሚዮች

**1.**አሰፋ ሃይሌ ገዝሙ

**2.**ማሞ ተሰማ አርአያ

**3.**አያሌው ማኑ ራያ ናቸው ።

እነዚህን ሰዎች የግንቦት ሰባት አባላት ናቸው ብሎ የሚነግረን ካለ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አልዋሹም ማለት ነው ፤ካልሆነ የተለመደው የግንቦት ሰባት ውሸት ነው ማለት ነው ።

4. ዶ/ብርሃኑ  ፀረ-ለውጥ ይሁንታዎችና ሃይሎች አስቀድሞ ማየት መቻል ፣የመረጋጌ/የጭር ግዜ ተግባራት፣የተቋማት ግንባታ ወዘተርፈ ያላቸውን 'መሪ አሳቦች' የተወሰዱት እላይ ከጠቀስኩት ከጂኒ ሻርፕ ጽሁፍ ነው ባይነኝ።

5.ይህ ጽሁፍ በየትኛውም አገር ከአምባ-ገነንአዊ ሥርዓት ወደ ዲሞክራሲይዊ ሥርዓት ሽግግር በሚደረግበት ግዜ መወሰድ ያለባቸውን ጥንቃቄዎች ያስገነዝባል። ከአገራችን የወቅቱ ሁኔታ ጋርም  እጅግ በጣም የተዛመደ ጽሁፍ ነው ።

6.በጣም የገረመኝ ዶ/ብርሃኑና ታማኝ ለመቀበል የወጣው ሕዝብ ብዛት ነው፣ ነፍስ ያለው ሚዲያ ስላላቸው ፥

ሀ) (በያንዳንዱ ስብሰባቸው የሚያደርጉትን ፀረ-ወያኔ ንግግራቸው፣በያንዳንዱ ሰላማዊ ሰልፎች የሚያስሙትን ፀረ-ወያኔ መፍከራቸው

ለ) ቦርጫቸውን ለመቀነስ (ሲሮጡ ፤ጂም ሲገቡ ፣ ዋና ሲዋኙ፣ ጤናማ  ምግብ ሲመገቡ ወዘተርፈ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ነጻ ለማውጣት በኤርትራ በርሃ  የትጥቅ ትግል ለማድረግ እየተዘጋጁ እንደሆ  ተደርጎ የሚቀርጹትን ምስሎች ፤በእሳት ሬዲዮና ቲቪ ስለሚያዳምጥና ስለሚያይ ይሆን?

ሐ)  ወይስ ወያኔ ከመጥላትና ወያኔ የተቃወመ ሁሉ ጅግና አድርጎ ከማየት? ይህም ቢሆን  ከአገር ውጭ ያሉ ወያኔ ተቃዋሚዮች፤የፈለገውን ያህል ጠንካራ  ቢሆኑ ሁነኛ ሚዲያ ከሌላቸው የአገር ቤቱ አውደ ሕዝብ ስለእነሱ የሚያውቅበት መንገድ የለውም ። ለምሳሌ የተቦጫጨቀና  እድፋማ  ልብስ ለብሰን ወደ አደባባይ ስንወጣና ሱፍና ከራባት ለብሰን ወደ አደባባይ ስንወጣ ያለው ልዩነት እንገምት ። ሱፍና ከራባት ለብሰን ስንወጣ ኖር የሚለን ይበዛል።

ስለሆነም ግንቦት 7 እና አጃቢዮቻቸው እርባና ያለው ትግል ስለታገሉ ሳይሆን ከላይ እንደገለጽኩት ፤ ያንን ያህል ሕዝብ ያስደመመላቸው ሚዲያቸው ነው ። የኢትዮ-ዲያስፖራ ሚዲያ ጠቅልለው /በሞኖፖል ይዘው ስለነበረ ነው ። (እሳት ቲቪ ፣እሳት ሬዲዮ፣ከረንት አፌርስ፣አባይ ሚዲያ፣ይካድ ፎረም፣ተንሳኤ ሬዲዮ ሁሉ የግንቦት 7ን እንቅስቃሴ  --የፕሮፓጋንድ፣የቅስቀሳ፣የአሻሽጥ ፣የማስተዋወቂያ ወዘተ.. መሳርያዎች ነበሩ ፤ናቸው  ።

የአርበኞች ግንቦት **7** ወደ አገር ቤትሲገባ የነበረው ፍንደቃ **(euphoria)** ማስረጃዎች

ከላይ እንደገለጽኩት የአርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ መሪዮች አዲስ ሲገቡ፡-

-የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ያደረጉላቸው ደማቅ አቀባበል

-በዶ/ብርሃኑ ወላጆች ቤት የተደረገው የናጠጠ ድግስና ጭፈራ

-መርያቸው ዶ/በርሃኑ ነጋ በአዲስ አበባ ብሄራዊ ኳስ ሜዳ/ስታዲየም  ንግግር ሲያደርግ የነበረው ፡-

-የሕዝብ ብዛትና ሕዝባዊ አቀባበል

-የቲፎዞዎቻቸው ሆይታና ፉጨት

-የአዲስ አበባ እስታዲየም በሺዮች ባንድራዎቻችን መጌጥ

-በአዲስ አበባ ንፋስ እገዛ የሺዎች ባንድራዎቻችን መውለብለብ

-ስንኙና ቃናው ዶ/ብርሃኑ ከነበረበት ከቀድሞ ኢሕአፓ የወሰዱት ቢሆንም -'ላንቺ ነው አገሬ' በተሰኘው መዝሙራቸውና በዕልልታ ታጅበው ያያቸው ጠ/ምኒስተር አብይን ተፎካክሮ የሚያሸንፍ ብቸኛ የፖለቲክ ድርጅት ግንቦት 7  ነው የሚሆነው የሚል ታይታ አስጥቷቸዋል ። ባጭሩ ይህንን ከህሎታቸውና ገጽታቸው የአርበኞች ግንቦት **7**  የአገር ቤት ፍንደቃ**<euphoria>** እለዋለሁ።

ኢ**-**ፍንደቃው **<dysphoria**

የአርበኞች ግንቦት **7** የአገር ቤት የጫጉላ ፍንደቃ ብዙም ሳይጓዝ በሚከተሉት ምክንያቶች ወደ ኢ**-**ፍንደቃ ወም ሃዘን ተቀየረ።

**1.**'የለመደች ጦጣ ሁልግዜ ሽምጣጣ እንደሚባለው'   ከህሎታቸውን ከፍ ለማድረግ በጎንደር አምስት **<5>** ሺ ሠራዊት አልን ማለታቸው ውሸት መሆኑን በጋዜጠኛ ጌታቸው ሺፈራው በመጋለጡ

**2.**  ልደቱ አያሌው በ **1997** ዓ**.**ም የቅንጅት መከፋፈል ምክንያት እኔ አይደለሁም፣ ዶ**/**በርሃኑ ነው ፣ያንን ይሁንታ ግልጽ ለማድረግ ዶ**/**ብርሃኑን በሚዲያ ካልተፋለምኩ ብሎ ራስምታት ስለፈጠ   ረባቸው

**3.**አክራሪ የዳዊት ይብሳ ቄሮዎች የኢትዮጵያን ባንድራ አስወርደው በኦሮሞ ባንድራ ካልተካን፣የምኒልክንም ሃውልት ካላፈረስን  በማለት አዲስ አበባን ሲያተራምሱ ፣ ባሳዩት ኦሮሞአዊ ወገንተኝነት  ዓይነ ሥውሩ ቴዲ በሚያስተናግደው 'ዕርዮት' ሬዲ አማካኝነት በአዲስ አበባ ሕዝብ አስተያየት **-**በመቀጥቀጣቸውና በመፈጥፈጣቸው

**4.** ያንን ለማስተባበል ታማኝ በየነ በምላሱ፣ መሳይ ከበደ በብዕሩ ያደረጉትን የሚዲያ ዘመቻ ተቀባይነት በማጣቱ

**5.**ከበርካት አገር ገንጣይ ጠባብ ብሄርተኞች**(quazi or rogue nationalists )** ጋር ግንባር ለመፍጠር ላይ ታች ሲሉ ቆይተው አልሆን ሲላቸው ያገኙትን የአርበኞች ድርጅት ከጉያቸው መሽሎክ ብርክ ስለፈጠረባቸው

**6.**የግንቦት **7** ድርጅቱም ሆነ አባላቱ **-**ትልቅ አጋራቸው ያደርጉናል ብለው ባመኗቸውን የኦሮሞ ድርጅቶችና የዶ**/**አብይ መንግሥት ተሰዶ**/**ሃንት ተደርገው ወደ እሥር ቤት መወርወር ወዘተርፈ ኢ**-**ፍንደቃ፣ወይም መቅጸፍታዊ ድንጋጤ ወይም ታይታኒክ ሾክ ፈጠረባቸው ባይነኝ ። በይሁንታው አዝንላቸዋለሁ እንጂ አልደሰትም

**PDF** ለማንበብ ይህን ይጫኑት..

***http://www.ethiopanorama.com/wp-content/uploads/2018/09/Gene-Sharp-1.pdf***